

# ሐይቲ
# Haiti



ጠዋት ጸሐይ ወጥታ፣
ብርሃን ተሞልታ፤
ቀዬው ደጁ ደምቆ፣
ህይወትን ሰንቆ. . .፤
የፊቱን አሻግሮ. . .፣
ራዕዩን ቀምሮ፣
«ነገም ሌላ ቀን ነው» ብሎ ሳያበቃ፣
ዛሬ «ሌላ» ሆነበት ተፈጸመ፤ በቃ!

ሲራሯጥ ገሚሱ፣
ለዚያች የዕለት ጉርሱ፤
ልጁን ስሞ ወጥቶ፣
ሥራ ተሰማርቶ. . .፤
ሳይመለስ ከቶ. . .፤
ቤተሰብ ተቀምጦ፣
ጠረጴዛ ሞልቶ፣
ራት እየተበላ፣
ጣሪያ ተደፋበት. . .
የሰው ልጅ ተከላ።



ማን አሰበውና
ይህንን ፈተና፤
በሕመም በስቃይ. . .፣
በረሃብ በጠኔ. . .፣
ፍርስራሽ ተጭኖት፣
ሳምንት.. አሳለፈ. . .
የሰው ልጅ በመዐት።



አገር አማን አድሮ፣
አገር ሰላም ውሎ፣
ሳይታሰብ ድንገት፣
ባንዴ ከመ-ቅጽበት፣
እንዲህ. . . ሆኖ ቀረ የሐይቲ ዕጣ፣
ተፈጥሮ ሲቆጣ።

**ጌታቸው አበራ**
**ጥር 2002 ዓ/ም**
**(ጃንዋሪ 2010)**

---

የሰብአዊ መብት ተሟጋች የሆነው ኢትዮጵያዊው ኦባንግ ሜቶ፣ በቅርቡ በድረ-ገጾች ላይ ባሰራጨው የዕርዳታ ጥሪ ጸሑፉ ላይ «ሐይቲያውያን በችግራችን ጊዜ (1934 እ.ኤ.አ.) ከጎናችን ቆመው ነበር፤ እኛስ አሁን በችግራቸው ጊዜ ልንደርስላቸው አይገባምን..?» እንዳለው ሁሉ፤ እምንችል፣ በቀይ መስቀልም፣ በዩኒሴፍም. . . በኩል *የእርዳታ እጃችንን ዘርግተን*፣ ከሰቆቃው የቲቪ ምሥል ዕይታ በኋላ፣ *ሰላማዊ እንቅልፍ ተኝተን ለማደር እንሞክር።*